DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሞች

በትምህርት ዓመት 2022-2023፣ በ'ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ፕሮግራሞች (Out of School Time Programs (OSTP) ቁጥጥር የሚደረግለት፣ በ**55 ትምህርት ቤቶች** ውስጥ ፤ ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሞች ይሰጣሉ። በOSTP ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሞች ውስጥ የማይካፈሉ ትምህርት ቤቶች፣ ለተማሪዎች የራሳቸው የሆኑ ፕሮግራሞችን ሊሰጡ ይችሉ ይሆናል። ለተጨማሪ መረጃ፤ የተማሪዎን ትምህርት ቤት፣ እባክዎን ያነጋግሩ።

- **የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ምዝገባ፣ ሰኞ፣ ጁን (JUNE) 6 ቀን 2022፤ በ12 ዕኩለ-ቀን ይጀምራል።** ምዝገባው በስራ-ላይ የሚውለው፤ በኦንላይን ላይ **የ2022-2023 የትምህርት ቀን (school day) ምዝገባቸውን ላጠናቀቁ ተማሪዎች ነው።**
- **በዚህ የትምህርት ዓመት ውስጥ አዲስ-የሆነ ነገር! የኦንላይን የምዝገባ ዘዴውን፣ በሞባይል-ስልክ (cellular device)፣ በኮምፒውተር፣ ወይም በታብሌት (tablet) - ልታገኙት ትችላላችሁ።** እነዚህም ማናቸውንም ዲቫይሶች ማግኘት ካልቻሉ፣ በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ፣ ኮምፒውተሮች የሚገኙ-ይሆናል። መቼ መጥተው መመዝገብ እንደሚችሉ ለማወቅ፣ እባክዎን ወደ ትምህርት ቤትዎ ይደውሉ። የዲሲ የሕዝብ መጽሐፍት-ቤቶችም፣ ለሕዝብ ጥቅም የሚውሉ ኮምፒውተሮች አሏቸው።
- ከትምህርት በኋላ (afterschool) አስተማሪዎችን፣ ባለሙያተኞች (paraprofessionals)፣ እና ቦታውን-መሪዎች (site leaders)ን፣ **'OSTP' እየቀጠረ ነው።** መረጃዎች፣ እና ለማመልከቻ የሚሆን ማገናኛ (link) እዚህ ይገኛል: https://dcps.dc.gov/page/afterschool-position-overviews

### ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራም፣ መግለጫ



**የ'ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሞች' ምን ዓይነት አገልግሎት ይሰጣሉ?**

የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሞች፤ ተማሪዎች በቀለም ትምህርት እና ከስርዓተ-ትምህርት ውጪ (extracurricular) ማበልጸጊያ እንቅስቃሴዎች እና አዲስ የትርፍ-ጊዜ ማሳለፊያዎች (hobbies) እና ችሎታዎች ውስጥ ለመካፈል ዕድል ይሰጣቸዋል። የDCPS ተማሪዎች፣ ባለሙያተኞች (paraprofessionals)፣ እና ከትምህርት-በኋላ (afterschool) አጋር-ድርጅቶች፤ በርካታ ልዩ የሆኑ የፕሮግራም አሰጣጥ አማራጮችን ለተማሪዎች ይሰጣሉ።

ከፍተኛ-ጥራት ባለው ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) የፕሮግራም አሰጣጥ ውስጥ መካፈል፤ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን፣ የቀለም ትምህርት ስኬትን፣ የተመራቂዎችን ቁጥር፣ እና በመማር ላይ ያላቸውን አመለካከት ላይ ማሻሻልን እንዲሚያመጡ ተረጋግጧል። ሁለት ከግማሽ ሰዓታትን በከትምህርት-በኋላ ፕሮግራሞች ውስጥ በየቀኑ የሚማሩ ተማሪዎች፣ ከሁለት ወራቶች ጋር አቻ ሆኖ የሚመጥን የመማሪያ ጊዜን ያገኛሉ።

**ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሙ ሰዓታቶቹ፣ ምንድናቸው?**

ከትምህርት-በኋላ (afterschool) ፕሮግራሙ፣ የትምህርት ቀኑ ካለቀ በኋላ የሚጀምት እና፣ በእያንዳንዱ የሙሉ-ቀን ትምህርት (በትምህርት ቤትዎ ሌላ ማስታወሻ እስካልተገለጸ ድረስ) በ6:15 pm የሚያልቅ ይሆናል።

**በየትኛው ክፍሎች ውስጥ ያሉ መካፈል ይችላሉ?**

OSTP ፕሮግራሞች፣ ከPK3 እስከ 5ተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን - በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ፤ እና ከPK3 እስከ 8ተኛ ክፍል ድረስ - በትምህርት ካምፓሶች ውስጥ አገልግሎት ይሰጣል። በ'River Terrace'፣ ሁሉም የክፍል-ደረጃዎች ብቁ ናቸው። በ'Hart MS' እና በ'ጄፈርሰን አካዳሚ (Jefferson Academy) MS' ፕሮግራሙ፤ ከ6-8 ክፍሎችን አገልግሎት ይሰጣል። *በእያንዳንዱ ቦታ ውስጥ ሊሰጡ የሚችሉ የክፍል-ደረጃዎች - በየOSTP' ፕሮግራሙ ሊለያዩ ይችላሉ፤ ለተማሪዎ ልዩ የሆነውን የክፍል-ደረጃ ላይ አገልግሎት-ሰጪው የተኛው እንደሆነ ለመወሰን፣ እባክዎን ትምህርት ቤትዎን አነጋግሩ።* የታወቁትን በ55 *ትምህርት ቤቶች* ውስጥ የሚገኙ አገልግሎት-ሰጪዎችን ዘርዝረናል።

**ምግብ ይሰጣል?**

እራት (Supper)/መክሰስ (snack)፣ ለሁሉም ተማሪዎች ካለምንም ክፍያ፣ በነፃ ይሰጣል።

**ተማሪዬን እንዴት ማስመዝገብ እችላለሁ?**

- **ለሁሉም ቤተሰቦች፤ ከትምህርት-በኋላ (afterschool) ምዝገባው በኦንላይን የ2022-2023 የትምህርት ቀን ምዝገባቸውን ላጠናቀቁ ተማሪዎች ይከናወናል። የትምህርት ቤት ምዝገባ፣ በአሁኑ-ጊዜ የተጀመረ እና፣ በትምህርት ቤትዎ ውስጥ በ**https://enrolldcps.dc.gov/ **ላይ መጠናቀቅ ይቻላል። a**
- **ለOSTP ከትምህርት-በኋላ (afterschool) የሚጀመርበት ቀን፤ ሰኞ፣ ጁን (JUNE) 6 ቀን 2022፣ በ12 ዕኩለ-ቀን ይሆናል።**
- **የኦንላይን የምዝገባ ዘዴውን፣ በሞባይል-ስልክ (cellular device)፣ በኮምፒውተር፣ ወይም በታብሌት (tablet) - ልታገኙት ትችላላችሁ።** ከላይ የተጠቀሱትን ማንኛውንም ዲቫይሶች ማግኘት ካልቻላችሁ፣ በትምህርት ቤትዎ ውስጥ ኮምፒውተሮች ይገኛሉ። መቼ መጥተው መመዝገብ እንደሚችሉ ለማወቅ፣ እባክዎን ወደ ትምህርት ቤትዎ ይደውሉ። የዲሲ የሕዝብ መጽሐፍት-ቤቶችም፣ ለሕዝብ ጥቅም የሚውሉ ኮምፒውተሮች አሏቸው። ተመልከቱ: የአገልግሎት ሰዓታት እና ቦታዎች
- **የኦንላይን ምዝገባው፣ አንድ-ጊዜ ከተከፈተ በኋላ፣** ቦታዎቹ የሚሞሉት፣ መጀመሪያ የመጣውን-ቅድሚያ ቦታን በመስጠት (first-come first-served) አሰራር ይሆናል። ያሉት መቀመጫዎች ውሱን ናቸው፤ ስለሆነም እባክዎን በቅድሚያ ተመዝገቡ።

**እንደ-ማስታወሻነት፤ ወደ ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራም ውስጥ ከመመዝገብ *በፊት*፤ ለመደበኛ የትምህርት-ቀን፤ የትምህርት ዓመት 2022-23 የምዝገባ ቅጾችን አስገብተው የጨረሱ እና መረጃው በሲስተሙ (system) ውስጥ እስከ-ሚስተካከል (update እስከሚያደርግ) ድረስ፣ ሁለት የስራ-ቀናት መስጠት ያስፈልጋል።** ስለ በትምህርት ቤት ምዝገባ፣ ተጨማሪ መረጃዎችን እዚህ ያግኙ: https://enrolldcps.dc.gov/

- የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ምዝገባቸው እስከሚረጋገጥ ድረስ፣ ማንም-ልጅ በፕሮግራሙ ውስጥ ገብተው-እንዲማሩ አይፈቀድላቸውም።

**በOSTP ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ውስጥ፣ ለመመዝገብ ችግር ከገጠመኝ፣ ምን ማድረግ አለብኝ?**

እርዳታን ለመጠየቅ፤ ትምህርት ቤትዎን ሬጅስትራር፣ ወይም ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ፕሮግራሞች (Out of School Time Programs)ን በ afterschool.dcps@k12.dc.gov ውእይም በ(202) 442-5002 በመደወል ያነጋግሩ።

**የሚከፈል-ክፍያ አለው?**

ለOSTP ፕሮግራም፣ የጋራ-ክፍያ (co-payment) ሆኖ የነበረው ክፍያ፤ ለትምህርት ዓመት 22-23 የማይቀጥል እና ልጆች በነፃ ይካፈላሉ። በአንዳንድ-ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ በሌላ የከትምህርት-በኋላ (afterschool) ሰጪዎች ለተማሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ - በተወሰኑ ክፍሎች ውስጥ፣ ክፍያ-ሊጠይቁ ይችሉ ይሆናል። የታወቁትን በ55 ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ አገልግሎት-ሰጪዎችን ዘርዝረናል። ካለ-ምንም ክፍያ አገልግሎቶችን፣ ሁሉም የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ፕሮግራም፣ ላይሰጥ ይችላል።

**እንዴት ነው ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሙ የሚገመገመው?**

የ'OSTP' ፕሮግራም፤ አብዛኛውን ጊዜ የገንዘብ እርዳታውን የሚያገኘው፣ በ'21st Century Community Learning Center grant (21CCLC)'፣ ከስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE) ነው። የSY19-20 21CCLC ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) የትምህርት ዓመቱ ማለቂያ የግምገማ ሪፖርት በOSSE እና DCPS የተቀረፁ የፕሮግራም ዓላማዎችን የያዙ እና በDCPS OSTP ከትምህርት-በኋላ (afterschool) ፕሮግራም የቅርብ-ጊዜ የመረጃ-ስብስብ (data) ይዞ በተገኘው - በ2019-2020 የትምህርት ዓመት ውስጥ፣ እነዚህ ዓላማዎች ግባቸውን መምታት/አለመምታቱ ላይ ግምገማን ያደርጋሉ። በተጨማሪም፣ አቀራረቡ (presentation)፣ ስለ'21CCLC' እርዳታ፣ የፕሮግራም ስነ-ሕዝብ አወቃቀሮች ላይ፣ ከውጪ ግምገማ አድራጊ የተገኙ ቁልፍ ነገሮች፣ ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሙ ጥንካሬዎች፣ እና በSY21-22 ትኩረት በሚሰጣቸው ነገሮች ዙሪያ - ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ይዟል። ለSY21-22 የግምገማ ሪፖርት (evaluation report) የሚጠናቀቅበት-ጊዜ፣ በበልግ (Fall) 2022 መጨረሻው-አካባቢ ላይ ይሆናል። ጥያቄዎች፤ የ'21CCLC' እርዳታ፣ ባለሞያ ወደሆኑት - ወደ ማርጎ በርኪ (Margot Berkey) በmargaret.berkey@k12.dc.gov ሊላክ ይችላል።

**በDCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚፈልጉ - ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራም ሰጪዎች፣ የተሰጠ መረጃ https://dcps.dc.gov/page/dcps-partners**

**ስለ 'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)'፣ ለሚኖሯችሁ ሁሉም ጥያቄዎች፤ እባካችሁን - በሚከተለው አነጋግሩ:** ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ፕሮግራሞች (Out of School Time Programs): ስልክ (202) 442-5002 ወይም ኢሜል afterschool.dcps@k12.dc.gov

**ተያያዥነት-ያለው ይዘት:**

የDCPS አጋሮች

የዲሲ የሕዝብ መጽሐፍት ቤት ድህረ-ገጽ -- ሰዓታት እና ቦታዎች

የዓመቱ-መጨረሻ፣ የሪፖርት ማቅረቢያ (Report Presentation) ውጤቶች